የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አራተኛ ዓመት ቁጥር ፲፯
አዲስ አበባ ታህሳስ ፲፫ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

24th Year No.17
ADDIS ABABA 22nd December, 2017

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፬፻፳፩/፪ሺ፲ ዓ.ም

የኢትዮጵያ ብሔራዊ አክሬዲቴሽን ጽሕፈት ቤትን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ገጽ ፲ሺ፶

## Content

Regulation No.421/2017

Ethiopian National Accreditation Office Establishment Council of Ministers Regulation …………………………………..…...………….. -- Page 10050

**የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፳፩/፪ሺ፲**

## የኢትዮጵያ ብሔራዊ አክሬዲቴሽን ጽሕፈት ቤትን ለማቋቋምየወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፮/፪ሺ፰ (በአዋጅ ቁጥር ፱፻፵፪/፪ሺ፰ እንደተሻሻለ) አንቀፅ ፭ እና ፴፰ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ብሔራዊ አክሬዲቴሽን ጽሕፈት ቤትን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፳፩/፪ሺ፲" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

፩/ "አክሬዲቴሽን" ማለት አንድ የተስማሚነት ምዘና አካል የተወሰነ የተስማሚነት ምዘና ተግባር ለማከናወን የሚያስችል ብቃት ያለው መሆኑን በሚመለከት የሚሰጥ ምስክርነት ነው፤

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION NO. 421/2017**

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE ETHIOPIAN NATIONAL ACCREDITATION OFFICE

This Regulation is issued by the council of Ministers pursuant to Article 5 and Article 38 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 916/2016 (as amended by Proclamation No.942/2016).

## PART ONE

## GENERAL

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as the "Ethiopian National Accreditation Office Establishment Council of Ministers Regulation No. 421/2017".

### 2. Definitions

In this Regulation, unless the context otherwise requires:

1/ "accreditation" means attestation related to a conformity assessment body, conveying formal demonstration of its competence to carry out specific conformity assessment tasks;

፪/ “የተስማሚነት ምዘና” ማለት ምርት፣ የስራ ሂደት፣ የአሠራር ስርዓት፣ ሰው ወይም ድርጅት የሚመለከታቸውን ደረጃዎችና መስፈርቶችን ማሟላታቸውን ማረጋገጥ ነው፤

፫/ “የተስማሚነት ምዘና አካል” ማለት አክሬዲቴሽን ሊሰጠው የሚችል የተስማሚነት ምዘና አገልግሎት የሚሰጥ የፍተሻ ላቦራቶር፣ የኢንስፔክሽን ተቋም፣ የሠርተፍኬሽን ተቋም፣ የካሊብሬሽንና ቬሪፍኬሽን ላቦራቶር፣ የንጽጽር ፍተሻ እና የሪፈረንስ ማቴሪያል አዘጋጅና አቅራቢ አካል ነው፤

፬/ “ባለሙያ” ማለት መሪ አሰሰር፣ ቴክኒካል አሰሰር፣ ቴክኒካል ኤክስፐርት፣ አሰልጣኝ፣ የአክሬዲቴሽን ኮሚቴዎች አባል እና ለተለያዩ የጽሕፈት ቤቱ ስራዎች ሙያዊ አስተዋጽዖ የሚያደርግ ከጽሕፈት ቤቱ ሠራተኞች ውጭ ያለ ግለሰብ ነው፤

፭/ “አሰስመንት” ማለት ጽሕፈት ቤቱ በተስማሚነት ምዘና አካላት ላይ የተቀመጠላቸውን ደረጃዎች እና መስፈርቶች መሠረት በማድረግ በተወሰነ የሥራ ወሰን ብቃታቸውን ለማረጋገጥ የሚያደርገው ግምገማ ነው፤

፮/ “የክትትል አሰስመንት” ማለት ከዳግም አሰስመንት በስተቀር አክሬዲቴሽን የተሰጣቸው አካላት የብቃታቸውን ቀጣይነት ለማረጋገጥ በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ የሚደረግ አሰስመንት ነው፤

፯/ “አክሬዲትድ የሆነ ተቋም” ማለት በጽሕፈት ቤቱ ወይም በዓለም አቀፍ ላቦራቶሪ አክሬዲቴሽን ትብብር ተቋም ወይም በዓለም አቀፍ የአክሬዲቴሽን ፎረም ሙሉ አባል በሆነ የአክሬዲቴሽን ተቋም አክሬዲትድ የሆነ የተስማሚነት ምዘና አካል ነው፤

፰/ “አክሬዲቴሽን ሠርተፍኬት” ማለት በተወሰነ የሥራ ወሰን አክሬዲቴሽን አገልግሎት ማግኘቱንና አክሬዴትድ መሆኑን የሚያረጋግጥ ሰነድ ነው፤

፱/ “ተቀባይነት ያላቸው ሕጋዊ ሰነዶች” ማለት አክሬዲትድ በሆኑ ተቋማት የሚሰጡ ሪፖርቶች እና ሰርተፍኬቶች ሲሆኑ አክሬዲትድ በሆኑበት መስክ፣ ብቃታቸው በተረጋገጡ ባለሙያዎች የተፈረመ እና አክሬዲቴሽኑ ከተወሰነ በኋላ የወጡትን ይመለከታል፤

2/ "conformity assessment" means demonstration that specified standards and requirements relating to a product, process, system, person or body are fulfilled;

3/ "conformity assessment body (CAB)" means a body that performs conformity assessment services including testing laboratory, inspection body, certification body, calibration and verification laboratory, proficiency testing provider and reference material producers and that can be the subject of accreditations;

4/ "professional" means lead assessor, technical assessor, technical expert, trainer, accreditation committee’s member and those who make professionals contributions to the Office activities excluding staffs of the Office.

5/ "assessment" means a process undertaken by the Office to assess the competence of a conformity assessment body, based on particular standard(s) and/or other normative documents and for a defined scope of accreditation;

6/ "surveillance" means set of activities, except reassessment, to monitor the continued fulfillment of requirements for accreditation by accredited conformity assessment bodies;

7/ “accredited body” means an organization or facility that has been accredited by the Office or by the International Laboratory Accreditation Co-operation institute (ILAC) or accredited by a full member of International Accreditation Forum (IAF);

8/ "Accreditation Certificate" means a formal document or set of documents, stating that accreditation has been granted for the defined scope of activities;

9/ “acceptable legal document” means a document or test report issued by an accredited body within their approved accreditation scope and signed by a person deemed to be competent to do so by the Office and issued after their accreditation;

፲/ "የአክሬዲቴሽን ምልክት" ማለት አክሬዲትድ የሆኑ ተቋማት አክሬዲቲድ መሆናቸውን ለማረጋገጥ እና አክሬዲትድ በሆኑበት ወሰን እንዲጠቀሙበት በጽሕፈት ቤቱ የሚሰጥ ምልክት ነው፤

፲፩/"የአክሬዲቴሽን ወሰን" ማለት አንድ የተስማሚነት ምዘና አካል አገልግሎት ለመስጠት በተቀመጡ መስፈርቶችና ደረጃዎች ተገምግሞ ብቃቱ የተረጋገጠበት የአገልግሎት ወሰን ነው፤

፲፪/"ሚኒስቴር" ማለት የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ነው፤

፲፫/ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው ሴትንም ይጨምራል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የኢትዮጵያ ብሔራዊ አክሬዲቴሽን ጽሕፈት ቤት

### ፫. ስለ መቋቋም

፩/ የኢትዮጵያ ብሔራዊ አክሬዲቴሽን ጽሕፈት ቤት (ከዚህ በኋላ "ጽሕፈት ቤት" እየተባለ የሚጠራ) ሕጋዊ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ እንደገና ተቋቁሟል፡፡

፪/ የጽሕፈት ቤቱ ተጠሪነት ለሚኒስቴሩ ይሆናል፡፡

፫/ ጽሕፈት ቤቱ በሀገሪቱ ለተስማሚነት ምዘና ተቋማት የሦስተኛ ወገን የአክሬዲቴሽን አገልግሎት የሚሰጥ ብቸኛ ተቋም ነው፡፡

### ፬. ዋና መሥሪያ ቤት

የጽሕፈት ቤቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

### ፭. ዓላማ

ጽሕፈት ቤቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

፩/ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያለው ብሔራዊ የአክሬዲቴሽን ሥርዓት በመገንባት እና በመተግበር ለሀገሪቱ ምርቶች እና አገልግሎቶች የሚሰጡ የተስማሚነት ምዘና አገልግሎቶች ዓለም አቀፍ ተቀባይነት እንዲኖራቸው በማድረግ የሀገሪቱን የሀገር ውስጥና የወጪ ንግድ ማቀላጠፍ፤

10/"accreditation symbol" means a symbol issued by the Office to be used by the accredited conformity assessment bodies within their scope of accreditation;

11/ "scope of accreditation" means a scope of competence issued to specific conformity assessment body to provide accreditation service based on standards and requirements;

12/"Ministry" means the Ministry of Science and Technology;

13/any expression in the masculine gender includes the feminine.

## PART TWO

## ETHIOPIAN NATIONAL ACCREDITATION OFFICE

### 3. Establishment

1/The Ethiopian National Accreditation Office is hereby re- established by this Regulation as an autonomous Federal Government office having its own legal personality.

2/The Office shall be accountable to the Ministry.

3/The Office is recognized as the sole third party National Accreditation Body for conformity assessment bodies.

### 4. Head Office

The office shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere, as may be necessary.

### 5. Objectives

The Office shall have the objectives to:

1/enhance export and inland trade of the country by establishing and implementing internationally recognized accreditation system and thereby causing issuance of internationally acceptable accreditation certificate for the goods and services of the country;

፪/ ብሔራዊና ዓለም አቀፋዊ ደረጃዎችና መስፈርቶችን በመጠቀም ለተስማሚነት ምዘና ተቋማት በሚሰጥ የአክሬዲቴሽን አገልግሎት የሕብረተሰቡ ጤና፣ ደህንነት፣ አካባቢ እንዲጠበቅ ማድረግ እና ፍትሐዊ የግብይት ሥርዓት እንዲሰፍን የበኩሉን አስተዋጽኦ ማድረግ፤

፫/ በአገር ውስጥ የሚደረግ የግብይት ቁጥጥርና መንግስታዊ ውሳኔዎች ውጤታማ፣ ተቀባይነት እና ተዓማኒነት ያላቸው እንዲሆኑ የበኩሉን አስተዋጽኦ ማድረግ፡፡

## ፮. ሥልጣንና ተግባር

ጽሕፈት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ ለተስማሚነት ምዘና አካላት አግባብነት ባላቸው ብሔራዊና ዓለም አቀፋዊ መስፈርቶች መሠረት በብቸኝነት ገለልተኛ የአክሬዲቴሽን አገልግሎት መስጠት፤

፪/ አክሬዲቴሽንን ለማስተዋወቅ በአክሬዲቴሽን ደረጃዎች፣ አሰስመንት ስልቶች እና ተዛማጅ መስፈርቶች ላይ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያለውን አሰራር ተከትሎ ሥልጠናዎችን መስጠት፤

፫/ የአክሬዲቴሽን ምልክት የአጠቃቀም መመሪያዎችን ማዘጋጀት፣ ማስፈጸም፣ በተጨማሪም በአባልነቱ የሚያገኘውን የአህጉራዊ፣ ዓለም አቀፋዊ የአክሬዲቴሽን ምልክቶች ፈቃድ ዓለም አቀፍ አሰራሩ በሚፈቅደው መሠረት ተዋውሎ አክሬዲትድ ለሆኑ ተቋማት መስጠት፤ አፈፃፀሙን መከታተል፤

፬/ የተስማሚነት ምዘና አካላት የአክሬዲቴሽን አገልግሎት እንዲያገኙ ማበረታታት፤ የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች ማስተዋወቅ፤ ስለአክሬዲቴሽን የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን መሥራት፤

፭/ አክሬዲቴሽን የተሰጣቸውን፣ የታገደባቸውንና የተሰረዘባቸውን አካላት ዝርዝር መዝግቦ መያዝ፤ ለሕዝብ ግልጽ ማድረግ፤ እንዲሁም ለሚመለከታቸው የሕግ አስፈፃሚ አካላት ማሳወቅ፤

2/ play its role to ensure the public health, consumer safety, environmental safety and fair market competition by providing competent accreditation service for CABs by using national and international standards;

3/ contribute its role to the efficiency and effectiveness of domestic market regulation, and government decision to enhance acceptance and confidence in the general public.

## 6. Powers and Duties

The Office shall have the powers and duties to:

1/ act as sole independent body to provide accreditation service to conformity assessment bodies based on national and international standards and requirements;

2/ promote accreditation by providing training on accreditation standards, assessment techniques and related requirements in an internationally acceptable manner;

3/ issue rules on how to use National Accreditation Symbol and ensure its implementation; promote and protect other legally granted regional and international umbrella organization symbols in an internationally acceptable way;

4/ promote and encourage conformity assessment bodies to obtain accreditation service; promote the service it provides and create awareness to clients on the benefit of accreditation;

5/ keep register and publicize the list of accredited bodies and those whose accreditations have been suspended and withdrawn, and notify same to the concerned regulatory bodies;

፮/ የአክሬዲቴሽን ሂደት የሚመራበትን በተለይም አመልካቾች የሚገመገሙበትንና አክሬዲቴሽን የሚሰጥበትን፣ የሚታገድበትንና የሚሠረዝበትን እንዲሁም ከዚሁ ጋር የተያያዙ ቅሬታዎች የሚስተናገዱበትን ሥርዓት የሚመለከቱ መመሪያዎችን ማውጣትና በሥራ ላይ ማዋል፤

፯/ አክሬዲትድ የሆኑ ተቋማት በአገኙት የአክሬዲቴሽን ወሰን ላይ በቀጣይነት ብቃታቸውን ማረጋገጣቸውንና የተቀመጡ መስፈርቶችን የማሟላት ኃላፊነታቸውን መወጣታቸውን ለማረጋገጥ የታቀደ ወይንም ድንገተኛ የክትትል አሰስመንት ማድረግ፤

፰/ የአክሬዲቴሽን ሰርተፍኬትና የአክሬዲቴሽን ምልክት ያለ አግባብ ጥቅም ላይ እንዳይዉል እንዲሁም የአክሬዲቴሽን መረጃ ባልተገባ መልኩ እንዳይተረጎም ክትትል ማድረግ፤ የተፈጠሩ ችግሮች እንዲስተካከሉ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን የመውሰድ፤

፱/ በሥራ አጋጣሚ በደንበኛ ላይ የሚደርሱ የንብረት ጉዳቶችን ለመሸፈን የመድህን ዋስትና የመግባት፤

፲/ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች በመንግስት በሚወሰን ተመን መሠረት የአገልግሎት ዋጋ ማስከፈል፤

፲፩/ የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋልና በራሱ ስም የመክሰስ ወይም የመከሰስ፤

፲፪/ሀገራችን ከገባቻቸው ዓለም አቀፍ ግዴታዎች ጋር የማይጣረሱ ስምምነቶችን ከሌሎች አካላት ጋር ማድረግ፤

፲፫/ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ማከናወን፡፡

## ፯. <u>የጽሕፈት ቤቱ አቋም</u>

ጽሕፈት ቤቱ፡-

፩/ የአክሬዲቴሽን ምክር ቤት (ከዚህ በኋላ “ምክር ቤት” እየተባለ የሚጠራ)፤

፪/ በመንግስት የሚሾሙ አንድ ዋና ዳይሬክተርና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፤ እና

፫/ አስፈላጊው ሠራተኞች

ይኖሩታል፡፡

6/ issue and implement directives governing the accreditation process, in particular, the assessment of applicants and the granting, suspending and withdrawing of accreditations, and handling of grievances relating thereto;

7/ conduct planned and surprise surveillance visit to verify continuation of scope of competence of accredited conformity assessment bodies and fulfillment of mandatory requirements issued by the Office;

8/ conduct supervision to protect misuse of accreditation certificate, accreditation symbol including misrepresentation of data from an accreditation; and take administrative measures to rectify problems identified;

9/ cause conformity assessment bodies to purchase insurance policy to cover any damage that they may cause on properties of clients during their activities;

10/ charge fees for the services it renders in accordance with the rate fee approved by the Government;

11/ own property, enter in to contract, sue and be sued in its own name;

12/ conduct agreements with other bodies that do not conflict with any international agreements that the country had entered in to.

13/ carry out other related activities necessary for the attainment of its objectives.

## 7. <u>Organization of the Office</u>

The Office shall have:

1/ a Council of Accreditation (herein after the "Council");

2/ a Director General and, as may be necessary, Deputy Director Generals to be appointed by the Government; and

3/ the necessary staff.

**፰. የምክር ቤቱ አባላት**

፩/ ምክር ቤቱ በሚኒስትሩ አቅራቢነት በመንግስት የሚሰየሙ አግባብ ካላቸው መንግሥታዊ አካላትና ከግሉ ዘርፍ የተውጣጡ አስፈላጊው የአክሬዲቴሽን ልምድና እውቀት ያላቸው ሰብሳቢውን ጨምሮ ከ ፲ እስከ ፲፭ አባላት ይኖሩታል፡፡

፪/ የጽሕፈት ቤቱ ዋና ዳይሬክተር የምክር ቤቱ አባልና ፀሐፊ ሆኖ ያገለግላል፡፡

፫/ የምክር ቤቱ አባላት የአገልግሎት ዘመን ፭ ዓመት ሲሆን በድጋሚ አንድ ጊዜ ለተጨማሪ አምስት ዓመት ብቻ ሊመደቡ ይችላሉ፡፡

**፱. የምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባር**

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ በጽሕፈት ቤቱ ተዘጋጅቶ የሚቀርብለትን የአክሬዲቴሽን ስትራቴጂዎች በመገምገም ያፀድቃል፤

፪/ ከባለድርሻ አካላት የሚነሱ ከአክሬዲቴሽን ጋር ተያያዥነት ባላቸው የፓሊሲና ስትራቴጂ ጉዳዮች ጽሕፈት ቤቱን ያማክራል፤

፫/ አክሬዲቴሽንን በሚመለከቱ ውሳኔዎች ላይ የሚቀርቡለትን ይግባኞች መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፤

**፲.የምክር ቤቱ ስብሰባ**

፩/ ምክር ቤቱ በሦስት ወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያካሂዳል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሰብሳቢው ጥሪ በማንኛውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያካሂድ ይችላል፡፡

፪/ የምክር ቤቱ አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡

፫/ የምክር ቤቱ ውሳኔ የሚተላለፈው በአብላጫ ድምፅ ሲሆን፣ ድምጽ እኩል ለዕኩል ከተከፈለ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

፬/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ሥርዓት መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል፡፡

**8. Members of Council**

1/ The Council shall have 10 up to 15 members including the Chairperson, to be drawn from the relevant government bodies, private sectors having relevant experience and knowledge relating to the functions and be nominated by the Minister assigned by the Government.

2/ The Director General shall participate in meetings of the Council as member and secretary.

3/ The term of office of the members of the Council shall be five years; provided, however, that they may be assigned for one additional five year.

**9. Powers and Duties of the Council**

The Council shall have the powers and duties to:

1/ review and approve accreditation strategies developed by the Office;

2/ advise the Office on policy and strategic issues raised by stake holders relating to accreditation;

3/ examine and decide on pleadings lodged against decisions with respect to accreditation.

**10. Meetings of the Council**

1/ The Council shall hold its regular meet every three months; provided, however, it may hold extraordinary meeting at any time when called by the chairperson.

2/ There shall be a quorum when majority of the members of the Council are present at a meeting.

3/ Decisions of the Council shall be passed by a majority vote; in case of a tie, the chairperson shall have a casting vote.

4/ Without prejudice to the provisions of this Article, the Council may adopt its own meeting rules and procedure.

**፲፩.የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር**

፩/ ዋና ዳይሬክተሩ የጽሕፈት ቤቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን የጽሕፈት ቤቱን ሥራ ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ ላይ የተመለከቱትን የጽሕፈት ቤቱን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የጽሕፈት ቤቱን ሠራተኞች በፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ሚኒስቴር ሕጎች መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ)የጽሕፈት ቤቱን የስራ ፕሮግራምና በጀት ያዘጋጃል፤ በመንግሥት ሲፈቀድም በስራ ላይ ያውላል፤

መ) አክሬዲት ለሆኑ ተቋማት የአክሬዲቴሽን ሰርተፍኬት ፈርሞ ይሰጣል፤

ሠ)ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ጽሕፈት ቤቱን ይወክላል፤

ረ) የጽሕፈት ቤቱን የሥራ አፈፃፀምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፡፡

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ ለጽሕፈት ቤቱ የሥራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለጽሕፈት ቤቱ ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

**፲፪.በጀት**

የጽሕፈት ቤቱ በጀት በመንግሥት ይመደባል፡፡

**፲፫.የሂሳብ መዛግብት**

፩/ ጽሕፈት ቤቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል፡፡

፪/ የጽሕፈት ቤቱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

**11. Powers and Duties of the Director General**

1/The Director General shall be the chief executive officer of the Office and shall direct and administer the activities of the Office.

2/Without limiting the generality of sub-article (1) of this Article, the Director General shall:

a) exercise the powers and duties of the Office specified under Article 6 of this Regulation;

b) employ and administer employees in accordance with the Ministry of Federal Public Service and Human Resource Development laws;

c) prepare and submit to the Ministry the work program and budgets of the office and implement same upon approval by the Government;

d) issue accreditation certificate to the accredited institutions;

e) represent the Office in its dealings with third parties;

f) prepare and submit the performance and financial reports of the Office to the Ministry.

3/The Director General may delegate part of his powers and duties to other officers and employees of the Office to the extent necessary for the efficient and effective implementation of the activities of the Office.

**12. Budget**

The Office's budget shall be allocated by the Government.

**13. Books of Accounts**

1/The Office shall keep complete and accurate books of accounts.

2/The books of accounts and financial documents of the Office shall be audited annually by the Auditor General or by auditors designated by him.

## ክፍል ሶስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፲፬.የአክሬዲቴሽን ተጠቃሚ በሆነ ተቋም ስለሚሰጡ ሪፖርቶች እና ሰርተፍኬቶች

አክሬዲትድ በሆኑ ተቋማት የሚሰጡ ሪፖርቶች እና ሰርተፍኬቶች አክሬዲትድ በሆኑበት መስክ፣ ብቃታቸው በተረጋገጠ ባለሙያዎች የተፈረመ ከሆነና አክሬዲትድ ከሆኑ በኋላ የወጡ ከሆኑ ተቀባይነት ያላቸው ሕጋዊ ማስረጃዎች ናቸው፡፡

### ፲፭.ሚስጥር ስለመጠበቅ

ማንኛውም በአክሬዲቴሽን ተግባር ላይ የተሳተፈ ሰው በሥራ አጋጣሚ ያገኛቸውን መረጃዎች ከሚከተሉት በስተቀር ለሌሎች አካላት መግለጽ የለበትም፦

፩/ ለጽሕፈት ቤቱ፤

፪/ ለጉዳዩ ባለቤት፤

፫/ በፍርድ ቤት በመረጃነት የተጠየቀ እንደሆነ፤

፬/ መረጃው አግባብነት ባለው መንግስታዊ ተቋም ለተቋማዊ ሥራ ወይም ለወንጀል ምርመራ የተፈለገ እንደሆነ፤

፭/ ለምክር ቤቱ ሰብሳቢ፡፡

### ፲፮.ክልከላ

በአክሬዲቴሽን አሰስመንትና በአክሬዲቴሽን አጽዳቂ ኮሚቴ አባልነት የሚሰማራ ባለሙያ በተስማሚነትና ምዘና የማማከር ሥራ መስራት የለበትም፡፡

### ፲፯.የመተባበር ግዴታ

፩/ አክሬዲትድ የሆኑ ተቋማትን ብቃት ቀጣይነት ለማረጋገጥ ጽሕፈት ቤቱ ለሚያከናውነው የታቀደ ወይንም ድንገተኛ የክትትል አሰስመንት ተቋማቱና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

፪/ ተቆጣጣሪ ተቋማት፣ ብሔራዊ ሥነ-ልክ ኢንስቲቲዩት እና የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ ከጽሕፈት ቤቱ ጋር የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

## PART THREE
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 14. Admissibility of Certificates and Reports

Certificates and reports issued by an accredited body after their accreditation as per their approved accreditation scope and signed by a competent person authorized by the Office to do so shall be considered legally admissible evidence.

### 15. Confidentiality

Any person who is involved in the performance of any function in relation to accreditation shall not disclose any information which he or she obtained in the course of performance of such a function except to:

1/ the office;

2/ the concerned party;

3/ if required by any court of law;

4/ any competent public authority for work, or for criminal investigation;

5/ the chairperson of the Council.

### 16. Prohibitions

Professional assessors and accreditation approval committee members shall not involve on the consultancy activities of conformity assessment bodies. •

### 17. Obligation to Cooperate

1/ Any accredited body and other concerned parties shall have the duty to cooperate with the Office for conducting planned and surprise surveillance visit to verify continued competence of accredited conformity assessment bodies.

2/ Regulatory bodies, National Metrology Institution and the Ethiopian Standards Agency shall have obligation to cooperate with the Office.

**፲፰.ስለ አክሬዲቴሽን ሠርተፍኬት አሰጣጥና አጠቃቀም**

፩/ አክሬዲቴሽን ሰርተፍኬት አክሪዲት ለሆኑ ተቋማት የሚሰጠው በጽሕፈት ቤቱ ዋና ዳይሬክተር ወይም እርሱ በሚወክላቸው ኃላፊዎች ተፈርሞ ይሆናል፡፡

፪/ ትክክለኛው የአክሬዲቴሽን ሠርተፍኬት በሕግ ፊት የሚፀናው በሰርተፍኬቱ ላይ የተገለፁትን የብቃት ወሰኖች በተመለከተ ብቻ ይሆናል፡፡

፫/ የአክሬዲቴሽን ሰርተፍኬቱ ንብረትነቱ የአክሬዲቴሽን ጽሕፈት ቤት ሲሆን ደንበኛው ሠርተፍኬቱን እንዲመልስ ሲጠየቅ የመመለስ ግዴታ አለበት፡፡

**፲፱.የተሻረ እና ተፈጻሚነት የማይኖረው ደንብ**

፩/ የኢትዮጵያ ብሔራዊ አክሬዲቴሽን ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፸፱/፪ሺ፭ በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

፪ ይህን ደንብ የሚቃረን ሌላ ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ ደንብ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**፳.ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታህሳስ ፲፫ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስቴር**

**18. Utilization of Accreditation Certificate**

1/ An accreditation certificate issued to the accredited institutions shall be signed by the Director General or persons delegated by him to do so.

2/ A certificate of accreditation issued in accordance with sub-article (1) of this Article shall be valid as evidence within the scope of competence contained therein.

3/ An accreditation certificate is the property of the Office and shall be returned by an accredited body when requested by the Office in case of failure to maintain requirement.

**19. Repealed and Inapplicable Regulations**

1/ The Ethiopian National Accreditation Office Establishment Council of Ministers Regulation No. 279/2005 is hereby repealed.

2/ No regulations, directives or practice shall, in so far as they are inconsistent with the provision of this Regulation, be applicable with respect to matters provided for by this regulation.

**20. Effective Date**

This Regulation shall enter in to force on the date of its publication in the *Federal Negarit Gazette.*

**Done at Addis Ababa, This 22nd day of December, 2017.**

**HAILEMARIM DESSALEGN**

**PRIME MINSTER OF THE FEDERAL DEMOCRATICEREPUBLIC OF ETHIOPIA**